# ፔንዱለም

ከጌትነት (ኖርዌይ)

ወለም ዘለም ወለም ዘልም
ለበስመአቡም አቋም የለም
ይብቃ እንግዲህ ሃቁ ይቅደም

ሰዓቱ መቁጠሩን
መሮጡ መፍጠኑን
ቆሞ አለመጠበቁን
እያውቀ ህሊናችን
እየተረዳ ልቦናችን
ብናውገረግር ብንመነዝር
ይትማሪሁ እውር ለእውር
ከንቱ መደናግር ማጭበርበር

የተስነጠቀ ሽክና
ለጠላ አይሆንምና

በሃቅ ላይ ከሚሸምቅ
ወዲህ ወዲያ ከሚንፏቀቅ
እዚያው ፈሶ እዚያው ይለቅ
ስንተዋወቅ አንተናነቅ

ሃቅ ያንቃል አይቀርም
ማስመሰሉም አያዋጣም
ሁለት እግር አለን ብንልም
ሁለት ዛፍ ላይ አይወጣም

መጃጃል ግምኛ
ከቶ ላይጠቅም ለኛ

ፈጥኖ ማሰብ መወሰኑ
ላልቀረለት መቧደኑ

ጎራው እንደሁ ለይቷል
መተማመን ቀርቷል
የአጅሬው ምሰሶ መሠረቱ ላልቷል
የእሥረኞቹ ድብዛ ጭራሹኑ ጠፍቷል
በእንዲህ ያለ ዘመን በእንዲህ ያለ ጊዜ
አይተኙም ይነቋል